**የጌተርስበርግ የመፅሀፍ በአል ሜይ 17 ለመከታተል ፕላን አድርጉ**

የMontgomery County Public Schools በጌተርስበርግ የከተማ አዳራሽ ግቢ ቅዳሜ፣ ሜይ 17 ለጌተርስበርግ የመፅሀፍ በአል (GBF) አጋር እንደሚሆን ሲያበስር ኩራት ይሰማዋል። GBF በሁሉም እድሜ ለሚገኙ ተማሪዎች የሚሆን ታላቅ ደራሲዎችና ድርጊቶችን እያሰለፈ ነው። በርካታ የMCPS ህብረተሰብ አባላት በበአሉ ንባቦች ያካሂዳሉ እናም ብዙ ፕሮግራሞች፣ ዎርክሾፖች፣ እና በንባብና በፅሁፍ ፍላጎትን ለማዳበር የተተለሙ የChildren's Village (የልጆች መንደር) ክንዋኔዎች ተካተዋል። ከልጆችና ከወጣት አዋቂ ደራሲዎች እንዲገኙ ፕሮግራም ከተያዘላቸው መካከል Rachel Renee Russell (ራቼል ሬኒ ረሰል) የ"The Dork Diaries" ተከታታይ ፅሁፎች ደራሲ፣ የስእላዊ ልቦለድ ደራሲ Raina Telgemeirer (ሬይና ተጌማየረር)፣ እና James L. Swanson (ጄምስ ስዋንሰን)፣ ተሸላሚው የፕሬዚዴንታዊ ታሪክ ፀሀፊ ይገኙበታል። የተወሰኑ ዎርክሾፖች የሚሸፍኑት የኮሌጅ መግቢያ መጣጥፎችን፣ ልቦለድ ፅሁፍ፣ ግጥም፣ እና የኩምክና ፈጠራን የሚሸፍኑ ናቸው።

ስለ GBF ተጨማሪ መረጃዎች gaithersburgbookfestival.org/ ተመልከቱ።

**የJohn Poole MS መምህር የ2014-2015 የMCPS የአመቱ መምህር ተብላ ተሰየመች**

John Poole Middle School የምትገኝ አንዲት የስምንተኛ-ክፍል መምህር የ2014-2015 የMontgomery County Public Schools (MCPS) የአመቱ መምህር ሆነናለች እናም አሁን ለሜሪላንድ የአመቱ መምህር ለመሆን ትወዳደራለች።

Jane Lindsay (ጄይን ሊንድሰይ) የአመቱ መምህር ተብላ የተሰየመችው በChampions for Children Awards Celebration (የልጆች ቻምፒዮኖች ሽልማት በአል) ነው። ወ/ሮ Lindsay፣ ከሶስቱ የአመቱ መምህር የመጨራሻ ተወዳዳሪዎች አንዷ የነበረችው፣ በPoole የ8ኛ ክፍል የእንግሊዘኛ እና የምንባብ መምህር ስትሆን፣ እና የክፍሉም ሀላፊ ናት።

QuickNotes mcps

የልጆች ቻምፒዮኖች ሽልማት በአል በMontgomery County Business Roundtable for Education (የንግድ ድርጅቶች የጠረፔዛ ዙሪያ ለትምህርት) (MCBRE) አማካይነት የሚስተናገድ ነው፣ ሊከናወን ያስቻለውም በደጋፊዎች ቸር ስጦታዎች ነው። MCBRE፣ ሙያቸውን ከMCPS አመራር ጋር የሚጋሩና ተማሪዎች በትምህርት ክፍል የሚማሩትንና ተጨባጩን አለም የሚያገናኙ ፕሮግራሞችን የሚደግፉ አንጋፋ የንግድ ስራ መሪዎችን የያዘ ለትርፍ የማይሰራ በጎአድራጎት ድርጅት ነው።

ወ/ሮ Lindsay ለMCPS ከ1988 ጀምራ ያገለገለች ናት በJohn Poole Middle Schoolም ባለፉት አምስት አመት አስተምራለች። በRocky Hill Middle School እና በStrawberry Knoll Elementary Schoolም አስተምራለች። ወ/ሮ Lindsayን ለምርጫ የሰየሟት፣ ተማሪዎች በትምህርታቸው እንዲያተኩሩና የስነ ፅሁፍ ክህሎቶች እንዲያተርፉ ለማገዝ ፈጠራዊ መንገዶች ማግኘትን ያሚያካትት፣ የማስተማር ሙያዋን አጉልተው ጠቁመዋል።

ው/ሮ Lindsay የተመረጠችው ከሶስት የመጨረሻ ዙር እጩዎች ነው፣ ሁሉም ደግሞ የMarian Greenblatt Education Fund Veteran Teacher Award (የማርያን ግሪንቤልት የአዛውንት መምህር ሽልማት ጥሪት) ተሸላሚዎች ነበሩ። ሌሎቹ የመጨረሻ ዙር እጩዎች Kathryn Hageman (ክትሪን ሀገማን)፣ በDiamond Elementary School የ5ኛ ክፍል መምህር እና Aaron Shin፣ በParkland Middle School የ8ኛ ክፍል መምህር ናቸው።

የMCPS የአመቱ መምህር የመጨረሻ ዙር እጩዎች ከMarian Greenblatt Education Fund $1,000 ይቀበላሉ። በተጨማሪ $1,000 በKaiser Permanente እና በChoice Hotels፣ እንዲሁም በMicrosoft Surface ታብሌት የቀረበ ይቀበላሉ። የMCPS የአመቱ መምህር እንደመሆንዋ፣ ወ/ሮ Lindsay ለአንድ አመት ከFitzgerald Auto Malls በቀረበ መኪና ትገለገላለች።

[በተጨማሪ ይማሩ]

**QuickNotes mcps**

## የMCPSን College Prep Fair (የኮሌጅ ዝግጅት በአል) እና Special Education Summit (የልዩ ትምህርት ከፍተኛ ጉባኤ) ይቀላቀሉ

*Leading the Way Today* (ዛሬ መንገዱን መምራት)፣ *Partnering for a Better Tomorrow* (ለተሻለ ነገ መሻረክ) በሚሉ ርእሶች ትኩረት በሚያደርገው የልዩ ትምህርት ከፍተኛ ጉባኤ እንዲገኙ የMCPS ወላጆች፣ ሰራተኞች እና የማህበረሰብ አባሎች ተጋብዘዋል። ከፍተኛ ጉባኤው ቅዳሜ፣ ሜይ 17 ከ 8:15 a.m.–2:30 p.m. Rockville High School, 2100 Baltimore Road in Rockville ይከናወናል።

ነፃው ክውነት ስንክልና ላላቸው ተማሪ ቤተሰቦች መገልገያዎችና ዎርክሾፖች ያቀርባል። ቤተሰቦች በተጨማሪ ከብዙ የMCPS ፅ/ቤቶች እና የMontgomery County ወኪል ድርጅቶች እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ተውካዮች ጋር የመገናኘት እድል ይኖራቸዋል።

ለከፍተኛ ጉባኤ ለመመዝገብ Parent Academy website (የወላጅ አካዴሚ ድርጣብያ) ይጎብኙ ወይም 301-517-5940 ይደውሉ። የህፃናት እንክብካቤ፣ ቀላል ቁርስ እና የምሳ ባኮ ይቀርባሉ።

**ነፃ የኮሌጅ ዝግጅት እና የስኮላርሺፕ በአል ቅዳሜ፣ ሜይ 10 ከ1-4 p.m.፣** በUniversities at Shady Grove, 9630 Gudelsky Drive in Rockville ይከናወናሉ። በአሉ ኢላማ የሚያደርገው ከ6ኛ እስከ 10ኛ ክፍል የሚገኙ ተማሪዎችንና ወላጆቻቸውን ነው። ተሳታፊዎች የተለያዩ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ለማግኘት፣ ስለ የፋይናንስ እርዳታና ስኮላርሺፕ እድሎች እና መረጃያዊ የእረፍት ስብሰባዎች ለመከታተል እድል ይኖራቸዋል። እንዲሁም የUSG ካምፐስ/ግቢ ጉብኝትም ይኖራል።

መመዝገብ የተሻለ ይሆናል ይህም በMCPS Parent Academy (የወላጅ አካዴሚ) በኩል ሊፈፀም ይችላል። ለተጨማሪ መረጃዎች Office of Community Engagement and Partnerships (የማህበረሰብ ተሳትፎና ሽርክናዎች ፅ/ቤት) በ301-279-3100 ይገናኙ።

**የትምህርት ቦርድ የEthics Panel (የስነምግባር ጓድ) ክፍት የስራ ቦታ ለመሙላት አመልካች ይፈልጋል**

የMontgomery County የትምህርት ቦርድ ለባለ አምስት አባል የEthics Panel (የስነምግባር ጓድ) አንድ ክፍት ቦታ ለመሙላት ይፈልጋል። ክፍት ቦታው ከጁላይ 1 2014 ጀምሮ ለሶስት አመት የአገልግሎት ጊዜ ነው። አመልካቾች የMontgomery County ነዋሪዎች መሆን አለባቸው። አባላት በነፃ ነው የሚያገለግሉት።

ከጓዱ/ቡድኑ ሃላፊነቶች መካከል፡ (1)የትምህርት ቦርድ የስነምግባር መመርያ መተርጎም እና ስለ ትግባሬው የምክር አስተያየቶች ማውጣት፤ (2) በተፈጸመ ወንጀል ለሚቀርብ ቅሬታ ችሎት መስማት፤ እና (3)የፋይናንስ መግለጫ ፎርሞችን ማፅደቅ።

ከጓዱ/ቡድኑ አባላት በስራ ላይ የሚገኙ የትምህርት ቦርድ አባላት፣ የት/ቤት ሹማምንት፣ ሰራተኞች ወይም በትምህርት ቦርድ ቁጥጥር ስር የሚገኝ ድርጅት ቅጥር፣ ወይም የነዚህ ግለሰቦች የትዳር ጓደኞች መሆን አይችሉም። ጓዱ/ቡድኑ በአመት አንድ ጊዜ በመገናኘት የፋይናንስ መግለጫ ፎርሞችን ድህረ እይታ ያደርጋል እንዳስፈላጊነቱም የምክር አስተያየት ቅሬታዎችንና ጥያቄዎችን ይገመግማል።

አመልካቾች ፍላጎታቸውን የሚገልፅ ደብዳቤ ከአጭር የህይወት ታሪክ ወይም ማመልካቻውን ከሚደግፍ ሌላ ሰንድ ጋር በስራ መዝጊያ ወቅት አርብ፣ ሜይ 30 2014 ገቢ ማድረግ አለባቸው፣ ይህም  በጁን 17 2014 የቦርድ ስብሰባ ላይ ለቀጠሮ መወሰኛ ይሆናል። (አመልካቾች በዚህ ስብሰባ ላይ መካፈል አይኖርባቸውም።) የፍላጎት ደብዳቤና አጭር የህይወት ታሪክ ለSuzann King, Montgomery County Board of Education, 850 Hungerford Drive, Room 123, Rockville, Maryland 20850 ይላኩ።
Suzann_M_King@mcpsmd.org

ለተጨማሪ መረጃ፣ 301-279-3617 ደውሉ።

Ethics Panel (የስነምግባር ጓድ)

**የ2014 የወላጅ ተሳትፎ በልዩ ትምህርት ዳሰሳ ጥናት**

ልዩ ትምህርትና የተያያዙ አገልግሎቶች በመቀበል ላይ ያሉ ልጆች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች የሜሪላንድ የወላጅ ተሳትፎ በልዩ ትምህርት ዳሰሳ ጥናት እንዲፈፅሙ ይጠየቃሉ። የምትሰጧቸው መረጃዎች በህዝብ ት/ቤቶች የሚቀርቡ ልዩ ትምህርትና የተያያዙ አገልግሎቶችን ለማሻሻል ስቴቱ የሚያደርገውን ጥረት ለመምራት ያግዘዋል። የዳሰሳ ጥናቱ ስም-የለሽ ነው መስመር ላይም መፈፀም ይቻላል። የዳሰሳ ጥናቱን መፈፀሚያ የጊዜ ገደብ አርብ፣ ሜይ 30 2014 ነው።

ጥናቱን ይውሰዱ

**ስለ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ማግኔት ኮንሰርቪየም ተጨማሪ ይማሩ**

የ4ኛ ክፍል ተማሪ ወላጆች ስለ ሶስት Middle School Magnet Consortium (መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ማግኔት ኮንሰርቪየም) (MSMC) የት/ቤት አማራጮችና የ*Choice* (ምርጫው) ሂደት ለመማር በመረጃያዊ ስብሰባ እንዲገኙ ተጋብዘዋል። *Choice* (ምርጫው) የሚከናወነው በተማሪው/ዋ 5ኛ አመት በፎል ወራት ነው። ስብሰባው የሚካሄደው ሮብ፣ ሜይ 9፣ በ7 p.m. Montgomery High School, 250 Richard Montgomery Drive in Rockville ነው።

Middle School Magnet Consortium (መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ማግኔት ክንሰቪየም)

**እንዲሁም...**

ወላጆች፣ በElementary Immersion Program መቀመጫ ለመቀበል የጊዜ ገደቡ አርብ፣ ሜይ 9 መሆኑን አትርሱ። ማስታወቂያ ደብዳቤዎች በኤፕረል መጨረሻ ላይ በፖስታ ተልከዋል።

**የተማሪ መኪናና ኮምፒውተር ሽያጭ ቀን ሜይ 10 እንዲውል ተወሰነ**

የትምህርት አመቱ በተማሪ የሚመራ የመጨረሻው ሽያጭ አያምልጣችሁ። MCPS Automotive Trades Foundation and Information Technology Foundation (የመኪና ንግዶች በጎአድራጎት እና የመረጃ ቴክኖሎጂ በጎአድራጎት) የሚገኙ ተማሪዎች የታደሱ መኪኖችና ኮምፒውተሮች ቅዳሜ፣ ሜይ 10 በ9 – 11 a.m. Thomas Edison High School of Technology, 12501 Dalewood Dr. in Silver Spring ይሸጣሉ። ለሽያጭ የሚቀርቡት ዕቃዎች ከትምህርት ክፍል ጥናቶቻቸው በተያያዘ መንገድ በተማሪዎች ተፈትሸዋል።

ስለ መኪኖች መረጃዎች Mike Snyder (ማይክ ስናይደር) በ301-929-2164 ደውሉለት። ስለ ኮምፒውተሮች መረጃዎች John Brewer (ጆን ብርወር) በ301-929-6975 ደውሉለት። ገቢዎቹ ለMontgomery ተማሪዎች የመኪና ንግዶች በጎአድራጎት እና የመረጃ ቴክኖሎጂ በጎአድራጎት ጥቅም ላይ ይውላሉ።

Automotive Trades Foundation
(የአውቶሞቢሎች ንግድ ስራ ተቋም)
Information Technology Foundation
(የመረጃ ቴክኖሎጂ በጎአድራጎት)